DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# በቅድመ-መዋዕለሕፃናት እና መዋዕለሕፃናት ምዝገባ፣ ማለፊያዎች/Promotions፣ እና ማቆያዎች/Retentions ላይ፤ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (Frequently Asked Questions) - ለወላጆች እና አሳዳጊዎች

**የተሰጠበት ቀን: ዲሴምበር (December) 6 ቀን 2022**

## የቅድመ-መዋዕለሕፃናት ምዝገባ እና ወደሚቀጥለው ክፍል ማለፍ/Promotion

1. **በቅድመ-መዋዕለሕፃናት ውስጥ ልጄን እንዴት ነው ማስመዝገብ የምችለው?**
የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (District of Columbia Public Schools (DCPS) - ነፃ፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው፣ የሙሉ-ቀን የቅድመ-መዋዕለሕፃናት (Pre-K) ትምህርትን፣ በሁሉን የዲሲ ዋርዶች/Wards ዙሪያ ዕድሜያቸው ሦስት- እና አራት ዓመት ለሆኑ ልጆች፤ ይሰጣል። በዋሽንግተን ዲሲ የሚኖር ማንኛውም - ዕድሜው ለትምህርት-የሚያስገድደው ተማሪ፣ ቢያንስ በመጀመሪያ-ደረጃ፣ በመካከለኛ (middle) ደረጃ፣ በከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት— እነርሱን በማንኛውም ጊዜ መግባት በሚያስችላቸው ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ባለው የተማሪ አድራሻ መሠረት አድርጎ፣ በማንኛውም-ጊዜ በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ቢያንስ አንድ፣ ገብቶ-የመማር መብት አለው። ሆኖም-ግን፤ የሦስት- እና የአራት ዓመት ዕድሜ ያላቸው በትምህርት-ቤት ተገኝተው የመማር መስፈርትን ማሟላት የሌለባቸው በመሆኑ-የተነሣ፤ የ'Pre-K3' እና 'Pre-K4' ክፍሎች በግዳጅ-መማር የማያስፈልጋቸው ክፍሎች የሆኑ እና ለእያንዳንዱ የ'Pre-K' ተማሪ፣ በየክልል-ወሰን ትምህርት ቤታቸው ውስጥ - DCPS ቦታ ስለማግኘታቸው ዋስትና-አይሰጥም።

   የ'Pre-K' የምዝገባ ሂደት የሚጀምረው፤ ከ'My School DC (MSDC) መደበኛ-የሆነ ማመልከቻ የሚጀምር፣ እና ምደባዎቹም የሚወሰኑት - ፍትሃዊ እና እኩልነት-ባለው የሎተሪ ስርዓት-ዘዴ በሆነው - በ'DC Office of the State Superintendent of Education (OSSE)' በሚተዳደረው አማካኝነት የሚካሄድ ነው። የሦስት- እና የአራት ዓመት ዕድሜ ያላቸውን በትምህርት-ቤት ውስጥ ገብተው ለመጀመሪያ-ጊዜ እንዲማሩ ለማድረግ፤ ሁሉም ቤተሰቦች - በ'MSDC' ሎተሪ አማካኝነት ማመልከት አለባቸው። ለተጨማሪ መረጃዎች፣ በwww.myschooldc.org ላይ ጎብኙ ወይም፣ የ'My School Dc'ን አፋጣኝ-መስመር (Hotline)ን በ202-888-6336 ደውሉ።

2. **ለ'Pre-K' ምዝገባ፣ የዕድሜ መስፈርቶቹ ምንድናቸው?**
ወደ 'Pre-K' እና የመዋዕለሕፃናት ፕሮግራሞች ለማስመዝገብ በሚድረግ ጥረት-ውስጥ፤ DCPS፣ በዕድሜ መስፈርቶቹ ላይ - በውስጥ ደንብነት በሚከተለው ሁኔታ በተገለጹት-መሠረት (5-E DCMR § 2004) በጥብቅ-ህጉን የሚከተል ይሆናል:
   - በትምህርት ዓመቱ ወቅት - በሴፕቴምበር (September) 30 ላይ ወይም ከዚያ-በፊት - የሦስት (3) ዓመት ዕድሜ የሚሆነው ተማሪ፤ ለ'Pre-K3' በትምህርት-ዓመቱ ውስጥ ብቁ-ይሆናል።
   - በትምህርት ዓመቱ ወቅት - በሴፕቴምበር (September) 30 ላይ ወይም ከዚያ-በፊት - የአራት (4) ዓመት ዕድሜ የሚሆነው ተማሪ፤ ለ'Pre-K4' በትምህርት-ዓመቱ ውስጥ ብቁ-ይሆናል።
   - በትምህርት ዓመቱ ወቅት - በሴፕቴምበር (September) 30 ላይ ወይም ከዚያ-በፊት - የአምስት (5) ዓመት ዕድሜ የሚሆነው ተማሪ፤ ለ'መዋዕለ-ሕፃናት/Kindergarten' - በትምህርት-ዓመቱ ውስጥ ብቁ-ይሆናል።

3. **ስለ ልጄ የዕድገት-ሁኔታ ያስጨንቀኛል፣ እና ለ'Pre-K' ዝግጁ-መሆናቸውን እርግጠኛ-አይደለሁም። ምን-ማድረግ አለብኝ?**
ልጅዎ፤ እንዴት እንደሚራመድ፣ እንደሚያወራ፣ እንደሚጫወት፣ እንደሚማር፣ ወይም ባለው ባህሪው ላይ ስጋቶች ካሏችሁ፤ ይህን ነገር ሲያድጉ ያልፉታል በማለት እስከ 'Pre-K' እስከሚጀምር-ድረስ አትጠብቁ። ልጅዎ ሁለት-ዓመት ከስምንት-ወራት ከሆነው፤ እባካችሁ የ'DCPS Early Stages'ን በ(202) 698-8037 ወይም www.earlystages.org በማነጋገር፤ በዕድገት-ላይ ያለውን ሂደት ለመመርመር (developmental screening) እንዲቻል፤ እባካችሁ አነጋግሩ። ልጅዎ - ከሁለት ዓመት-ከስምት ወራት በታች ከሆነ፤ የ'OSSE's Strong Start'፣ የ'DC Early Intervention' ፕሮግራምን፣ በ(202) 727-3665 ወይም በwww.eip.osse.dc.gov እባካችሁ፣ አነጋግሩ።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

4. **ልጄ፣ የ‘Pre-K’ የክፍል-ደረጃን መዝለል ያለበት ይመስለኛል። በሚቀጥለው የክፍል-ደረጃ ውስጥ እንዲገባና እንዲማር ማድረግ እችላለሁ?**
በጥያቄ #2 ላይ በተገለጸው መሠረት፤ DCPS፣ በዕድሜ መስፈርቶቹ ላይ - በውስጥ ደንብነት በተገለጹት-መሠረት በጥብቅ-ህጉን የሚከተል እና በዚህም-ምክንያት - ከ‘Pre-K3 ወደ ‘Pre-K4’ ወይም ደግሞ ከ‘Pre-K4’ ወደ መዋዕለሕፃናት/Kindergarten - የዕድሜ መስፈርቶቹ የተሟሉለት ካልሆነ በስተቀረ - የመዘዋወር-ዕድሎች አይፈቀዱም። ይህም ማለት፤ ለDCPS አዲስ የሆኑ ተማሪዎች እና የ‘Pre-K3 ወይም ‘Pre-K4’ ቦታቸውን በ‘MSDC’ ሎተሪ አማካኝነት ያገኙ፤ ወደ ሚቀጥለው የክፍል-ደረጃ በትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ከመዘዋወራቸው በፊት፣ የተመዘገቡበትን የክፍል ደረጃ ማጠናቀቅ ይገባቸዋል-ማለት ነው። <u>እባክዎን ያስታውሱ: የዕድሜው የማቆሚያ-ገደብ (cutoffs) ሆነው ከተቀመጡት ከእነዚህ ዕድሜዎች ጋር ጎን-ለጎን የሚሄድ የልደት-ቀን ለሌለው ልጅ - የ‘Pre-K’ የሎተሪ ቦታን ያመለከቱ እና ያገኙ ቤተሰቦች፤</u> — <u>ለምሳሌ፤ ለ‘Pre-K4’ ቦታን ለማግኘት - የ‘Pre-K3’ ዕድሜ-ያለው ልጅ ካመለከተ</u> — <u>ቦታውን የሚያጣ እና ወደ ትክክለኛው የክፍል-ደረጃ በ‘MSDC’ አማካኝነት እንደገና-ለማመልከት የሚመራ-ይሆናል።</u>

## <u>የመዋዕለሕፃናት ምዝገባ እና በግዳጅ-መሰጠት ያለበት ትምህርት (Compulsory Education)</u>

5. **አንድ-ልጅ፣ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ መማይ የሚያስፈልገው-መቼ ነው?**
በዲሲ ሕግ-መሠረት፤ የትምህርት ዓመቱ በሚጀመርበት-ጊዜ ላይ - እስከ ሴፕቴምበር (September) 30 ድረስ፣ ልጁ ዕድሜው አምስት ሆኖ (ወይም በዚህ-በተጠቀሰው ቀን የሚሞላው)፤ ሁሉም በዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ልጆች፤ ትምህርት በሚሰጥበት ትምህርታዊ-ተቋም ውስጥ ገብተው መማርን ይጠይቃል። ይህ መስፈርት፤ ‘በግዳጅ ገብቶ-መማር (compulsory attendance)’ ተብሎ-ይጠራል። DC Code § 38-202(a). አስፈላጊ-ለሆነው በትምህርት ቤት ተቋማት ውስጥ ተገኝቶ-መማር - ብቸኛ ለየት-ያለ ሁኔታን ሊፈጥር የሚያስችለው መንገድ፤ ወላጆች እና አሳዳጊዎች፣ በመኖሪያ-ቤት ውስጥ ማስተማር (homeschool)ን ለልጃቸው ለማድረግ ለሚፈልጉ እና፣ ከ ‘OSSE’ ጋር - በመኖሪያ-ቤት ውስጥ ማስተማር (homeschool)ን ለማድረግ-ፍላጎት እንዳላቸው ፋይል-ካደረጉ ብቻ ነው። ስለ በቤት-ውስጥ ማስተማር (homeschooling) መስፈርቶች፤ ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፤ በ https://osse.dc.gov/service/homeschooling-district-columbia ላይ፣ እባካችሁ ተመልከቱ።

6. **ልጄን በመዋዕለሕፃናት/Kindergarten ውስጥ እንዴት ላስመዘግብ እችላለሁ?**
በሴፕቴምበር (September) 30 ቀን ላይ፣ አምስት-ዓመት የሞላቸው ወይም ወደ አምስተኛ ዓመታቸው የሚሸጋገሩ ተማሪዎች፤ በክልል-ውሰናቸው ውስጥ (in-boundary) በሆነ የ‘DCPS’ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው በመዋዕለሕፃንት/Kindergarten ውስጥ የመማር መብት ያላቸው፣ እና በ‘MSDC’ አማካኝነት - ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቦታ-ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። በክልል-ወሰን ውስጥ (in-boundary) የሚገኘውን ትምህርት ቤትዎን ፈልገው ያግኙ: https://enrolldcps.dc.gov/node/41.

7. **ልጄ ለመዋዕለሕፃናት/Kindergarten፣ ዝግጁ-የሆነ አይመስለኝም። ለማስመዝገብ፤ ዕድሜያቸው 6 ዓመት እስከሚሆን - መጠበቅ እችላለሁ?**
በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ - በሴፕቴምበር (September) 30 ቀን ላይ፣ ዕድሜያቸው አምስት የሆናቸው (ወይም የሚሞላቸው) ልጆች፤ በትምህርታዊ-ተቋም ውስጥ ገብቶ-መማር ወይም መመዝገብ አለባቸው። በዲሲ ሕግ መሠረት፤ ትምህርታዊ-ተቋም (educational institution) ማለት፤ የ‘DCPS’ ትምህርት ቤት፣ የዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት፣ የግል-የሆነ (independent) ትምህርት ቤት፣ የቤተክርስቲያ ትምህርት ቤት፣ ወይም የግል-ትምህርት ሰጪ (private instructor) ማለት-ነው። DC Code § 38-201(2A).

ሆኖም-ግን፤ የልጅ የዕድገት ማዕከል (child development center)ን፣ የግል ቅድመ-ትምህርት ቤት፣ የመኖሪያ ቤት የልጅ-እንክብካቤ (home daycare)፣ ወይም ሌላ የቅድመ-ልጅነት ፕሮግራምን ውስጥ መማር፤ አስገዳጅ-የሆነው የትምህርት መስፈርት የሚያሟላ አይደለም።

8. **ልጄ፣ የ'መዋዕለ-ሕፃናት/Kindergarten'ን - መዝለል ያለበት ይመስለኛል። በ1ኛ ክፍል ውስጥ እንዲገባና እንዲማር ማድረግ እችላለሁ?**
   በጥያቄ #2 ላይ በተገለጸው መሠረት፤ DCPS፣ በዕድሜ መስፈርቶቹ ላይ - በውስጥ ደንብነት በተገለጹት-መሠረት በጥብቅ-ህጉን የሚከተል እና በዚህም-ምክንያት - የአምስት-ዓመት ዕድሜ ያላቸውን፣ የመዋዕለሕፃናት/Kindergarten - አጠናቅቀው-የጨረሱ ካልሆኑ በስተቀረ፤ ወደ አንደኛ-ክፍል ገብቶ-ለመማር አይፈቅድላቸውም።

   ሆኖም-ግን፤ በክፍል-ደረጃዎች ውስጥ - ከመዋዕለሕፃናት እስከ አምስተኛ ድረስ ተመዝግበው ለሚማሩ ተማሪዎች፣ የትምህርት-ዓመቱ ከተጀመረ በኋላ - ከመካከለኛ-ዓመት ልዩ ማዘዋወሪያ (mid-year special promotion)ን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ሂደት አለ። የበለጠ-ለማወቅ፤ የትምህርት ዓመቱ ከተጀመረ በኋላ፣ የልጅዎን ርዕሰ-መምህር - አግኝተው ለማነጋገር ይችላሉ።

<u>**በ'Pre-K' እና በመዋዕከሕፃናት ውስጥ፣ ወደ ሌላ-ክፍል ማለፍ (Promotion) እና በዚያው-መቆየት (Retention)**</u>

9. **ተማሪዬ፣ በ'DCPS ውስጥ - በ'Pre-K' ውስጥ ተምሯል፤ እና በክፍል-ደረጃቸው ውስጥ ደግመው እንዲማሩ እፈልጋለሁ። ይህ ሊሆን ይችላል?**
   DCPS፣ የቅድመ-መዋዕለሕፅናት ተማሪዎችን በዚያ-ማቆየት (retaining)፤ ወይም የ'Pre-K3 ወይም የ'Pre-K4'ን የተማሪዎችን-መድገም፤ በአጠቃላይ-አይደግፍም። ሆኖም-ግን፤ የ'Pre-K3፣ የ'Pre-K4፣ እና የመዋዕለሕፃናት ተማሪዎች፤ እዚያው-ሊቆዩ የሚችሉት - የመዘዋወር መስፈርቶችን የማያሟሉ ከሆኑ ((DC Official Code § 38-781.01(a)) ወይም፣ በ'Pre-K3፣ 'Pre-K4፣ ወይም መዋዕለሕፃናት ውስጥ የመድገት አማራጭ-ሊሰጣቸው የሚችለው - በዋና የትምህርት-ዓይነት ዙሪያዎች የላቀ-ብቃት መስፈቶችን የሚያሟሉ - ነገር-ግን በችሎታ-ደረጃቸው ማከናወን ባለመቻላቸው ለመዘዋወር - በአካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ወይም ስሜታዊ ዕድገት ዙሪያዎች (5-E DCMR § 2201.6) ዝግጁ-የማያደርጋቸው ከሆነ ነው። በጣም-አልፎ አልፎ በሚገጥም-ሁኔታ - ተገቢ-ሆኖ ሊገኝ በሚችልበት ሁኔታ ላይ፤ የ'Pre-K' ተማሪው በክፍል-ደረጃው ውስጥ እንዲደግም የመደረግ ውሳኔ - በተማሪው ርዕሰ-መምህር አማካኝነት ሊደረግ ይችላል (DC Official Code § 38-781.01(b)(1)) <u>እና</u>፣ ወላጅ መስማማት-አለበት። የተማሪው በዚያው-ክፍል እንዲቆይ ማድረግ (retained) - ከለ-ወላጅ የስምምነት-መስጫ መደረግ የማይችል፤ እና በዚያው-ክፍል እንዲቆይ በወላጅ የሚጠየቅ ጥያቄም፤ ካለ-ርዕሰ መምህሩ ስምምነት ሊሰጥ አይችልም።

10. **ልጄ በ'Pre-K' ውስጥ ተመዝግቦ እየተማረ ነው፤ ነገር ግን፣ በሚያሳዩት ሂደት ወይም ዕድገት ላይ ስጋት-አለኝ። በዚያው የክፍል-ደረጃ መድገም ይችላሉ?**
    ስለ ልጅዎ የመማር፣ የዕድገት፣ የንግግር-ችሎታ፣ ወይም ባህሪይ ስጋቶች ካሏችሁ፤ ወደ ልዩ ትምህርት (special education) ግምገማ እንዲደረግ - መምራት (referral)ን ማድረግ (ወይም መጠየቅ) ትችላላችሁ። ይህን ጥያቄ፤ ለልጅዎ አስተማሪ ወይም ለርዕሰ መምህሩ፤ በቃል ወይም በጽሁፍ መጠየቅ ትችላላችሁ። የልዩ ትምህርት (special education) ግምገማ ማስፈለግ-እና አለማስፈለጉን፤ ትምህርት ቤቱ የሚወስን እና፤ በውሳኔው ከመቀጠሉ በፊት የእናንተን-ስምምነት ይጠይቃል።

11. **የእኔ የ'Pre-K' ተማሪ፣ በ'Pre-K' ውስጥ እንዲቆይ ወይም ደግሞ-እንዲማር ከተደረገ፣ አሁን-ባሉበት የ'DCPS' ትምህርት ቤታቸው ውስጥ መቆየት ይችላሉ?**
    ሁሉም የ'Pre-K3' እና የ'Pre-K4' ቦታዎች የሚመደቡት - በ'MSDC' የሎተሪ ሂደት አማካኝነት በመሆኑ-ምክንያት፤ ሁሉም የ'Pre-K3' እና የ'Pre-K4' እዚያው-የማቆየት(retention)/የመድገም (repeating) ውሳኔዎች፤ በምዝገባ ላይ ተጽዕኖ-አድርገው ሊያመላክቱ ይችሉ-ይሆናል።

    የልጅዎ-ትምህርት ቤት፤ ለ'Pre-K' - ልጅዎ በሚደግምበት የክፍል-ደረጃ ውስጥ ቦታ ካለው፤ ልጅዎ እንደገና ተመልሶ ወደ 'MSDC' የሎተሪ ሂደት ውስጥ ሳይገባ - ባለው-ቦታ ላይ ተማሪዎ ለመመዝገብ ይችል-ይሆናል።

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

የልጅዎ-ትምህርት ቤት፤ ለ'Pre-K' - ልጅዎ በሚደግምበት የክፍል-ደረጃ ውስጥ ቦታ ከሌለው፤ ምዝገባዎች ወደ በጋ (summer) ጊዜ ተራዝሞ-የተገፉ ከሆነ፣ ልጅዎ ቅድሚያ እንዲያገኝ-ይደረጋል። ለልጅዎ ቦታ ሊገኝ-የማይችል ከሆነ፤ ትምህርት ቤቱ - ከDCPS ማዕከላዊ ቢሮ (Central Office) ጋር በመስራት፤ የ'Pre-K' ቦታ ሊገኝ-በሚችልበት በሌላ የDCPS ትምህርት ቢእት ውስጥ ለመመደብ-ይሰራል።

**12. ተማሪዬ፣ DCPS-ባልሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ በ'Pre-K' ውስጥ ተምሯል፤ እና በዚያው የክፍል-ደረጃቸው ደግመው እንዲማሩ እፈልጋለሁ። ይህ ሊሆን ይችላል?**

DCPS-ባልሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲማር-ለነበረ - በቅድመ-መዋዕለሕፃናት የክፍል-ደረጃ ውስጥ እንዲደግም - የወላጆች ጥያቄዎች፤ በDCPS ሊሰጥ-የሚችል አይሆንም። በጥያቄ #2 ላይ በተገለጸው መሠረት፤ በዕድሜ መስፈርቶች መሠረት-ባደረገ ሁኔታ፣ ተማሪዎች ይመዘገባሉ።

**ተጨማሪ የመረጃ-ምንጮች (Resources)**

- በክልል-ወሰን ውስጥ (in-boundary) የሚገኘውን ትምህርት ቤትዎን ፈልገው-ያግኙ:http://enrolldcps.dc.gov/node/41
- የ'My School DC': https://www.myschooldc.org/
- የ'DCPS የምዝገባ እና የሎተሪ የመመሪያ-መጽሐፍ (Enrollment and Lottery Handbook): https://enrolldcps.dc.gov/node/66
- የ'DCPS Early Stages': (202) 698-8037 ወይም referrals@earlystagesdc.org
- የ'OSSE Strong Start'፣ የ'DC Early Intervention' ፕሮግራም: (202) 727-3665 ወይም www.eip.osse.dc.gov
- SY21-22 Retention and Promotion Guidance
- OSSE Homeschool Program: https://osse.dc.gov/service/homeschooling-district-columbia
- ስለዚህ መምሪያ-ስለሆነ ሰነድ ጥያቄዎች ካሏችሁ: dcps.earlychildhood@dc.gov